# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

## የአስቸኳይ ሙስና መከላከል የማስፈጸሚያ ማንዋል/ UREGENT CORRUPTION PREVENTION MANUAL

uption manal




ጥር/ 2/ 5/2016 ዓ/ም

አዲስ አበ

- መውጫ

ራዕይ ........ 1
ተልዕኮ ........ 1
እሴቶች ........ 1
ክፍል አንድ ........ 1
1. መግቢያ ........ 1
1.1. የማንዋሉ መነሻ ሁኔታዎች/ ታሳቢዎች ........ 2
1.2. የማንዋሉ አጠቃላይ ዓላማ ........ 3
1.3. ዝርዝር ዓላማዎች ........ 3
1.4. የማንዋሉ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ........ 3
1.5. ከማንዋሉ የሚጠበቅ ውጤት ........ 4
1.6. የማንዋሉ የተፈጻሚነት ወሰን ........ 4
1.7. የቃላትና የጽንሰ ሃሳቦች ማብራሪያ/ትርጓሜ ........ 5
ክፍል ሁለት ........ 7
2. የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ምንነት፣የአሰራር መርሆዎች እና ጥናት አስፋላጊነት፣ ........ 7
2.1. የአሰቸካይ ሙስና መከላከል ምንነት ........ 7
2.2. የአስቸኳይ የሙስና መከላከል የአሰራር መርሆዎች ........ 7
2.3. የአስቸኳይ ሙስና መካከል ጥናት አስፋላጊነት፣ ........ 7
2.4. የአስቸኳይ የሙስና መከላከል የጥቆማ ጭብጥ መሰረታዊ መርህ ........ 8
2.5. አስቸኳይ ሙስና መከላከል ከሌሎች የሙስና መከላከል ጥናት የሚለይባቸው ባህሪያት ........ 8
2.6. መረጃዎችና ማስረጃዎችን እንዴት ማግኘት ይቻላል? ........ 8

urgent coruptin manal

ክፍል ሦስት ........................................................ 10
3. የአስቸኳይ ሙስና ከላከል ጥናት የአሰራር ሥርዓት ........................................................ 10
3.2. የአስቸኳይ የሙስና መከላከል የአሰራር ሥርዓት ........................................................ 11
3.3. የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት ሪፖርት ይዘቶች ........................................................ 12
3.4. የጥናት ሪፓርቱን ለበላይ ሀላፊ ለውሳኔ ማቅረብ ........................................................ 13
ክፍል አራት ........................................................ 13
4.የኮሚሽኑና የተቋማት የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ተግባርና ኃላፊነት ........................................................ 15
4.1.የኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነት ........................................................ 15
4.2.የተቋማት የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ተግባርና ኃላፊነት ........................................................ 16
አባሪዎች ........................................................ 17
የጥናትማድረጊያቅጽ፣የሪፓርት ቅጽ፣ተጠያቂ ........................................................ 17
አባሪ-1.የጥናት ማድረጊያ ቅጽ ........................................................ 17
አባሪ 2. የሪፓርት ማድረጊያ ቅጽ ........................................................ 19
አባሪ 3. ተጠያቂ የሆኑ የመንግስት አመራሮች፣ሰራተኞ ........................................................ 19
አባሪ-4 በአሰቸኳይ የሙስና መከላከል የዳነ ሀብት የሚሳለበት አግባብ ........................................................ 20
አባሪ-5. የአስቸኳይ ሙስና መከላከል የጥናት የጊዜ ስታንዳርድ መነሻ ........................................................ 20
ማጣቀሻዎች ........................................................ 22

urgent coruptin manal

## የኮሚሽኑ ራዕይ፣ተልዕኮ እና እሴቶች

### ራዕይ

በ2025 ሙስና ለከተማ አስተዳደሩ ልማት እና መልካም አስተዳደር እንቅፋት ከማይሆንበት ደረጃ ማድረስ፡፡

### ተልዕኮ

አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የስነ ምግባር እና የጸረ ሙስና ትምህርትን በማስፋፋት፣የአሰራር ስርዓትን በማጥናትና እንዲሻሻሉ በማድረግ፣ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላs ከል በመንግስት አሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ማድረግ፡፡

### እሴቶች

- ግልፅኝነት
- ተጠያቂነት
- ታማኝነት
- አብሮነት
- ድፍረት
- ፍትህ
- ዴሞክራሲያዊነት

urgent coruptin manal

# ክፍል አንድ

## 1. መግቢያ

ሙስና እጅግ አደገኛ ወንጀል በመሆኑ ለመፈጸም ከፍተኛ ዝግጅት እና ጥንቃቄ ተደርጎ የሚፈፀም ወንጀል ነው፡፡ ሙስና ከተፈፀመ በኋላ የሙስና ድርጊትን መመርመር፣ መክሰስ፣ ጥፋተኛ ማስባል፣ ማስቀጣት እና በሙስና የተዘረፈውን ሃብት ማስመለስ እጅግ ከባድ ስራ ነው፡፡ በመሆኑም ሙስና ከመፈፀሙ በፊት መከላከልን የመሰለ ውጤታማ ስራ የለም፡፡ ሙስና ከመፈፀሙ በፊት ከምንከላከልባቸው ዘዴዎች ውስጥ ደግሞ አስቸኳይ የሙስና መከላከል ዘዴ አንዱ ነው፡፡ አስቸኳይ ሙስና መከላከል ሙስና ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት ለመፈፀም ወይም እንደፈፀም ለማድረግ የሚደረግ ዝግጅትን ማምከን እና ወደ ውጤት እንዳይሻጋገር ማድረግ ነው፡፡

በመሆነም ሙስና እና ብልሹ አሰራር የከተማዋን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እድገት የሚጎዳ መሆኑን በመገንዘብ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በብቃት መዋጋት የሚችል እና የአሰራር ነጻነት ያለው ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስነ-ምግባርና የፀረ- ሙስና ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 75/2014 እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ ምንም እንኳ ኮሚሽኑ ከተቋቋመ አጭር ጊዜ ቢሆንም በስነ- ምግባር ግንባታውና ሙስና መከላከል ስራው በርካታ ተስፋ ሰጪ ስራዎችን አከናውኗል፤ከተቋቋመለት ዓላማ አንጻርም ጅምርና ተስፋ ሰጪ ውጤቶች አስመዝግቧል፡፡

በአጠቃላይ የተጀመረውን የስነ-ምግባር ግንባታና የሙስና መከላከለል ስራውን ለማስቀጠልና ይበልጥ ዘላቂነት ውጤታማነት ባለው መልኩ ለመምራት በተለይም ደግሞ የሙስና ተግባር ሳይፈጸም ወይም ለመፈጸም በሂደት ላይ እያለ በህዝብና በመንግስት ሀብት ላይ አስከፊ ጉዳት ከማድረሱ በፊት የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት በማካሄድ ውጤት ማስመዝገብ ይቻል ዘንድ ይህ ማንዋል ተዘጋጅቷል፡፡

የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት የሚደረገው ድርጊቱ በህግ ከተቀመጠው የአሰራር ስርዓት ውጭ እየተከናወነ ወይም በመከናወን ላይ ያለ መሆኑን በግልፅ የሚያሳይ መረጃ እና ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ሲገኝ፣በሂደቱ የመንግስትንና የህዝብን ሀብት ጉዳት ላይ ሊጥል የሚችል

መሆኑን ሲያመለክት ነው፡ጥናቱን ለማከናወን አጥኚው ሊኖሩት የሚገቡ ቴክኒካዊ ፣ሰብዐዊና ስነ ምግባራዊ ጉዳዮች በማንዋሉ የአሰራር ስራ ውስጥ ተካተዋል፡፡፡

በመሆነም የማንዋሉ ዋና ዓላማም በየደረጃው የሚገኙ የመከታተያ ክፍሎች በእውቀት፣ መረጃና ማሽረጃ እንዲሁም የጋራ መርሆዎችንና እሴቶች ላይ የተመሰረተ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት እንዲያደርጉ ለማስቻል ይህ የአሰራር ማንዋል እንዲዘጋጅ ሆናል፡፡

## 1.1. የማንዋሉ መነሻ ሁኔታዎች/ ታሳቢዎች

**አንደኛው መነሻ** ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የያዘውን የብልጽግና ጉዞ ማሳካት የሚቻለው በስነ-ምግባር የታነጸና ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የጸዳ ፐብሊክ ሰርቫንትና ህብረተሰብ መፍጠር ሲቻል ነው፡፡ ስለሆነም በተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶች ግልጽ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ፍትሃዊና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ሊሰጡ ይገባል፡፡በመንግስት መስሪያቤቶች በህዝብ ተቋማትና በልማት ድርጅቶችም የሚታየውን የሌብነትና ብልሹ አሰራር በመቀነስ ለተቋቋሙለት ዓላማ በጽናት እንዲሰሩ ማድረግ ይገባል፡፡

የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ እንዲሰራበት ለኮሚሽኑ የቀረቡ ጥቆማዎችን በጥናት በመለየት የግልጸኝነትና የተጠያቂነት ስርዓትን እያሰፈኑ መምራትን ታሳቢ በማድረግ ይህ የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት ማንዋል ተዘጋጅቷል፡፡

**ሁለተኛው መነሻ፡-** በአዋጅ ቁጥር 75/2014 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 4 ለኮሚሽኑ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በመንግስት መ/ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ሙስና ለመፈፀም የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ሲጠረጥር ወይም ጥቆማ ሲደርሰው ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት አስቸኳይ የሙሰና መከላከል ጥናት ስራ በመስራት ሂደቱ እንዲቋረጥና እንዲስተካከል እንደሚያደርግ ተደንግጓል፤ በመሆኑም ይህ ተግባር ከላይ እስከታች ያለው የስነ ምግባር አመራርና ፈጻሚ ተግባራዊ እንዲያደርገው አስገዳጅ በመሆኑ፡፡

**ሶስተኛ መነሻ፡-** ይህ የአሰራር ማንዋል የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት ላይ የነበረውን የግልፀኝነት ችግር በመፍታት በሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች፣ የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች ላይ ውጥ የአሰራር ስርዓት እንዲኖር በማድረግ ሙስና ብልሹ አስራሮችን ለመከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፣

urgent corruption manal

### 1.2. የማንዋሉ አጠቃላይ ዓላማ

የአስቸ ኳይ ሙስና መከላከል ጥናት እና የአሰራር ስርዓት ከላይ እስከ ታች ወጥ በሆነ መንገድ እንዲመራ በማድረግ **የግልፅኝነትና የተጠያቂነት ስርዓት ማስፈን ነው፡፡**

### 1.3. ዝርዝር ዓላማዎች

1) በከተማ አስተዳደሩ የመንግሰት መስሪያ ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ሙስና ለመፈፀም በሂደት ላይ የሚገኝን አንድ ለሙስናና ብልሹ ሽሽአሰራር የተጋለጠ አሰራር ቀድሞ በመከላከል የመንግስትና የህዝብን ንብረት ከብክነት እንዲድን ለማድረግ፤
2) በከተማ ደረጃ ወጥ የሆነ የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ትግበራ እንዲኖር ለማድረግ፣
3) በከተማ አስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ ሲሰሩ በግልፅነትና በተጠያቂነት መርህ መሰረት ስራውን እንዲያከናውኑ መሰረታዊ እውቀትና ክህሎትን የጋራ ግንዘቤ እንዲኖር፣
4) የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች በየተቋማቸው ውስጥ ውጤታማ የሆነ የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ በሚሰሩበት ወቅት ምን ምን ነጥቦችን አካተው መስራት እንዳለባቸው ለማሳየት እና እንዲሰሩ ለማስቻል፣
5) በኮመሽኑ አስቸኳይ የሙስና መከላከል የጥናት ሂደትና ቅደም ተከተል በማስቀመጥ ሥራቸውን በግልጽ በተቀመጠ አሠራር፣በውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ለማከናወን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር፣
6) የተቋማት የበላይ ኃላፊዎች ለዚሁ ስራ ድጋፍ የሚያደርጉበትን አቅጣጫዎችን ለማመላከት፡፡

### 1.4. የማንዋሉ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ

- በከተማ አስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች፣በልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች የሚገኙ የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ባለሙያዎች ዘንድ ያለውን የአቅም ክፍተት በመሙላት በእውቀት ላይ የተመሰረተ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል የጥናት እዲያደርጉ ለማስቻል፣
- ኮሚሽኑ ያስቀመጠውን ራዕይና ተልዕኮ ለመሳካት

Urgent corruption

- የሙስና መከላከል ስራን ተግባራዊ በማድረግ እና ሙስናን በመቀነስ ስነ-ምግባርን የተላበሱ አገልጋይ ተቋማትን ለመፍጠር
- የኮሚሽኑ ባለሙያዎች አስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት ከማደረጋቸው በፊት ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ እንዲያስችላቸው፣
- ኮሚሽኑን ለሚቀላቀሉ አዳዲስ ባለሞያዎች ያለባቸውን የተግባር ልምድ ክፍተት ለማስወገድ፣
- ተቋማት በአገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን በመቅረፍ የተወዳዳሪነት ብቃትን እንዲያጎለብቱ ያሚያስችል ድጋፍ ማድረግ እንዲችሉ፣
- በተቋማት ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት የአሠራር ግልፀኝነት እና ተጠያቂነት የበለጠ እንዲሰፍን ለማድረግ፣
- ከላይ አሰከታች ባሉ ተቋማጥ ወጥ የሆነ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናትን ተግባራዊ ለማድረግ፤

## 1.5. ከማንዋሉ የሚጠበቅ ውጤት

- አሰቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት አስራር ምንነት ፣ጥቅምና አስፍላጊነት ላይ ትክክለኛ የጋራ ግንዛቤ ይፈጠራል፣
- ባለሙያዉ አሰቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት አስራር ለማዘጋጀት አስፍላጊ የሆኑ ግባዓቶችን የአዘገጃጀት ሂደቶችን ላይቶ ያወቃል ፣
- ባለሙያው ለለ አሰቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት አስራር እና አዘገጃጀት በቂ ዕውቀትና ክህሎት ይኖረዋል፡፡
- በየደራጃው የሚገኙ ባለሙያዎች የአሰቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት ማዘጋጀት እና ማጥናት ይችላል፡፡
- የመንግስትና የህዝብ ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ያስችላል፡፡

## 1.6. የማንዋሉ የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ማስፈጸሚያ ማንዋል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 1.7. የቃላትና የጽንሰ ሃሳቦች ማብራሪያ/ትርጓሜ

**ሀ. አስቸካይ የሙስና መከላከል አገልግሎት ፡-** ማለት በአንድ ተቋም ውስጥ የተፈፀመ ያለን የአገልግሎት ወይም የእቃ ግዥን፣ቅጥር፣ደረጃ ዕድገት፣ምደባ ወይም ዝውውርን ወዘተ በሚመለከት የአሠራር ችግር አለ ተብሎ የሚቀርብ ጥቆማን መሰረት አድርጎ በሚደረግ የአሠራር ፍትሻ አሠራሩ ችግር ካለበት አፋጣኝ እርምጃ የሚወሰድበትን ጊዜያዊ መፍትሔ መጠቆምን ለወደፊቱም ለሙስና ወይም ለብልሹ አሠራር የተጋለጠው አሠራር እንዳይቀጥል ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ ነው፡፡

**ለ. "አስቸኳይ መስና መከላከል" ማለት** ከመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ከመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚመጡ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የሚመለከቱ ጥቆማዎችን፣ መረጃና ማስረጃን መሰረት በማድረግ ሙስና ከመፈፀሙ በፊት በሂደት ላይ ያለን ጉዳይ የማጣራት ጥናት ስራ በማከናወን ሂደቱ እንዲቋረጥ ወይም ማስተካከያ እንደዲደረግ በማድረግ አፈፃፀሙን መከታተል ነው፡፡

**ሐ. ''ጠቋሚ መረጃ"** ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራ መነሻ የሚሆንና በተለያየ የመረጃ ማሰባሰቢያ አግባብ ለኮሚሽኑ ወይም ለተቋማት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የሚቀርብ መረጃ ነው፣

**መ."ጥርጣሬ የሚያሳድር መረጃ"** ማለት ተቋሙ ከሚያከናውነው ተግባርና ኃላፊነት ጋር በተያያዘ በመከናወን እና እየተከናወኑ ባሉ ተግባራት የሕጎችና አሰራሮች ጥሰት እየተፈፀመባቸው ወይም ሊፈፀምባቸው በሂደት ላይ ስለመሆኑ የሚያመለክት መረጃ ነው፣

**ሠ. "ብልሹ አሰራር" ማለት** በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ከህብረተሰቡ ጥቅም ይልቅ ራስን በማስቀደም ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ሲባል የአሰራር መመሪያን ወደ ጎን በመተው የሚከናወን የአሠራር ችግር ወይም ክፍተት ነው፡፡

**ረ. "ለሙስና የተጋለጠ አሰራር"** ማለት የመንግሰት መ/ቤት ወይም የልማት ድርጅት ወይም ሕዝባዊ ድርጅት ባለሥልጣን ሠራተኛ የተሰጠውን ስልጣን ወይም ኃላፊነት ወይም ሀብትና ንብረት አለአግባብ በመጠቀም ለራሱ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን ጥቅም ለማስገኘት በሚችል መልኩ እንዲሰራ የተጋለጠ አሰራር ነው፡፡

urgent coruptin manal

**ሰ.“ሂደት” ማለት** አንድ የተለየ ሥራን ለማከናወን ሲባል ከጫፍ እስከ ጫፍ የሚሠሩ ተግባራትን የሚያጠቃልል ሂደት ነው፡፡

**ሸ. “የአሰራር ሥርዓት”** ማለት አንድ ሥራ ሊከናወን ሥራውን ለማከናውን የተቀመጡ ሂደቶች ፣መመሪያዎችን፣ፈጻሚ አካላትንና ያለውን ግንኙነት(በማን ፣እንዴት ፣ለምን መቼና የት ንደሚሠራ ፣ወዘተ…) የሚያመለከት ሥርዓት ነው ፡፡

**ቀ. “ምክረ ኃሳብ” ማለት** በመንግስት የመንግስት መ/ቤት፣በመንግስት የልማት ደርጅት እና በሕዝባዊ ድርጅት ውስጥ በኮሚሽኑ ወይም በተቋሙ የስነምግባር መከታተያ ክፍል አማካኝነት የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ ተሰርቶ መወሰድ ስላለበት የእርምት እርምጃ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብ የውሳኔ ኃሳብ ነው፣

**በ. “የዳነ ሀብት”** ማለት በሙስና ወይም በብልሹ አሰራር ሊመዘበር የነበረን የመንግስትና የሕዝብ ሀብት የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ በመስራት ማዳነ ማለት ነው፡፡

**ተ. “ትንተና”** ማለት የተሰባሰበውን መረጃ በመመርመርና በመፈተሽ ፣ጥናት የሚደረግበት ተግባር፣ሂደት ወይም ርዕሰ ጉዳይ ለምን እንደሚሠራ፣በማን እንደሚሰራ፣እንዴት እንዲሚሰራ ፣የት እንደ ሚሰራ ወዘተ በዝርዝር መለየት ማለት ነው፡፡

urgent corruption manual

# ክፍል ሁለት

## 2. የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ምንነት፣የአሰራር መርሆዎች እና የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት አስፈላጊነት፣

### 2.1. የአሰቸካይ ሙስና መከላከል ምንነት

አስቸኳይ የሙስና መከላከል በተቋማት ውስጥ ሙስና ለመፈፀም የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ሲገመት ወይም ሲጠረጠር ወይም ጥቆማ ሲደርስ ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት አስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ በመሥራት ሂደቱ እንዲቋረጥ ወይም እንዲመክን ወይም አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ ተግባር ነው፡፡

### 2.2. የአስቸኳይ የሙስና መከላከል የአሰራር መርሆዎች

ማንኛውም የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ የሚከተሉትን መርሆዎች መሰረት በማድረግ መከናወን ይኖርበታል፣

1. በበቂ እዉቀት፣
2. ገለልተኝነት፣
3. ሚስጥር መጠበቅ
4. ተዓማኒነት፦
5. የግጽኝነትናተጠያቂነት

### 2.3. የአስቸኳይ ሙስና መካከል ጥናት አስፋላጊነት፣

የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት አስፍላጊነት ተቋሙ ተልዕኮውን የሚያሳካበት የአሰራር ስርዓት ነው፡፡ የአሰራር ሥርዓት ደግሞ አንድን ጉዳይ ሥራውን ለማከናውን የተቀመጡ/ ሂደቶ ፣አዋጆች፣ደንቦች ፣መመሪያዎችን፣ፈጻሚ አካላትንና ያለውን ግንኙነት(በማን ፣እንዴት ፣ለምን መቼና የት እንደሚሠራ፣ወዘተ…)የሚያመለክት ነው፡፡የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት ውጤታማ የሆነ አሰራር ስርዓት እንዲዘረጋ ከማድረግ አንጻር ጥናቱ በጥንቃቄ የከተከናወነ ከሆነ ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡

urgent coruptin al

ኮሚሽኑ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት በመጠቀም ራዕይና ተልኮውን በብቃት እንዲወጣ ከሚያስችሉት አንዱ መሳሪያ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራዎችን በጥናት ላይ ተመስርቶ በማከናወን የመንግስትና የህዝብ ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል በማድረግ ሙስና የወንጀል ድርጊት ከመሆኑ በፊት ወይም አስቀድሞ የጥፋት አቅሙን ለማድከም /ለማሳጣት ያግዛል፡፡ የተቋማት አገልግሎት አሰጣጥም በግልፅነት ተጠያቂነት አሰራር እንዲመሩ፣ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እንዳይፈጸሙ ከተፈጸሙም የእርምት እርምጃዎችን እዲወስዱ እና የሙስና ወንጀል ተከስቶ ወይም ተስፋፍቶ የሚያስከትለውን ኢኮኖሚያዊ፤ማህበራዊ፤ከባቢያዊና ፖለቲካዊ ኪሳራን ለማስቀረት ከፍተኛ አስተዋጽዎ አለው፡፡

## 2.4. የአስቸኳይ የሙስና መከላከል የጥቆማ ጭብጥ መሰረታዊ መርህ

1. ድርጊቱ በህግ ከተቀመጠው የአሠራር ሥርዓት ውጭ በመከናውን ላይ በመሆኑ በግልጽ የሚያሳይ መረጃ ሆኖ ሲገኝ፣
2. በሂደቱ መንግስትንና ህዘብን ሀብት ጉዳት ላይ ሊጥል የሚችል መሆኑን ሲያመላከት
3. ሂደቱ ለህግ ናአሠራር ታቃራኒ በሆነ መንገድ በመፈጸም ላይ መሆኑ ማመላከት አለበት

## 2.5. አስቸኳይ ሙስና መከላከል ከሌሎች የሙስና መከላከል ጥናት የሚለይባቸው ባህሪያት

1. ሙስና ለመፈፀም የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ሲጠረጠር ወይም ጥቆማ ሲደርሰው ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት አስቀድሞ የሚከናውን ተግባር መሆኑ፣
2. ተግባሩ በፍጥነት የሚከናወን መሆኑ፣
3. በመረጃ አሰባሰቡ ሂደት ከተለመደው መረጃ አሰባሰብ ስርአት ለየት ያለ መረጃ የማሰባሰቢያ ስልትን ሊጠይቅ የሚችልበት አግባብ መኖሩ፣
4. በሙስናና ብልሹ አሰራር ላይ ብቻ የሚያተኩር መሆኑ፣ ተግባሩ እስኪጠናቀቅ ድርስ የክትትል የቁጥጥር እና የአቅጣጫ ድጋፍ በማድረግ የመከላከል ስራ በመስራት ውጤቱን የሚያስመዘግብ መሆኑ፣

## 2.6. መረጃዎችና ማስረጃዎችን እንዴት ማግኘት ይቻላል?

የሙስናና ብልሹ አሰራር ለመቅረፍ በሚደረግ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ማግኘት ለስራችን ውጤታማነት የማይተካ ሚና አለው ታብሎ ይታመና፡፡ስለሆነም በመንግስት መስራቤቶች፣በልማት ድርጀት ወይም በህዝባዊ ድርጅቶች

urgent coruption manal


ውስጥ ሙስና ብልሹ አሰራሮችን ተፈጽሟል ተብለው የሚጠረጠሩ ከሆነ በመጀመሪያ ከስራው ጋር ግንኙነት ካላቸውና ስለተፈጸመው ነገር እውቀት አላቸው ተብለው ከሚገመቱ ሰራተኞች ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ወይም በሌሎች አማካይነት በማመቻቸት ስለተፈጸሙ የሙስና ብልሹ አሰራሮችን መረጃ ዎችንና ፍንጮችን ለማግኘት ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ ማስረጃ የማሰባሰብ ስራ መስራት ለጥናት ውጤታማነት አስፍላጊ መሆኑን መረዳት ያስፍልጋል፡፡ችግሩን ለይቶ አስከፊ ጉዳት ሳያደርስ ማስተካከያ ለማድረግ ችግሩ የተከሰተበት ተቋም አመራር፣ፈጻሚ እና ባለድርሻ አካላት ሚናና ተሳትፎ ወሳኝ

urgent coruptin manal

# ክፍል ሦስት

## 3. የአስቸኳይ ሙስና ከላከል ጥናት የአሰራር ሥርዓት

የአስቸኳይ ሙስና መከላከል የጥናት ሁደት አንድን ጉዳይ በተለያየ አቀራረብና ዘዴ በማጥናት ምን ዓይነት የሙስና እና ብልሹ አስራር እንደተፈጸመ፣ማን እንደፈጸመው፣ ለምን እንደተፈጸመ፣ በድርጊቱ ወስጥ ተሳታፊ የሆኑ አካላትን ፣የሙስና እና ብልሹ አስራርን መቼና እንዴት እንደፈጸመው በማያጠራጥር ሁኔታ የሚተነትንበት እና የሚያጣራበት ሂደት ነው፡፡ ስለሆነም ጥናት ሲደርግ እነዚህ ተግባራት ግምት ወስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ የቀረበ ጥቋማን መቀበል፣ እግድ ማዘጋጀት ፣የድርጊት መርሐ ግብር ማዘጋጀት ፣ ጥናት ማካሄድ ፣ ትንተናና የመፍትሄ ሀሳብ ሪፓርት ማዘጋጀትና ማጽደቅ፣ ጥናቱን መገምገም እና የትግባራና እገዛ ድጋፍ ማድረግ ነው፡፡




urgent coruption manal

## 3.2. የአስቸኳይ የሙስና መከላከል የአሰራር ሥርዓት

አስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ ሆን ተብለው በሚፈፀሙ አለያም ባለማወቅ ወይም በአቅም ማነስ ምክንያት የሚፈፀሙ ስህተቶችን ቀድሞ ለማረምና አስፈላጊውን የማስተካከያ እርሚጃ ለመውሰድ ዓይነተኛ መሣሪያ መሆኑን መገንዘብ ያስፍልጋል፡፡ በመሆኑም ውጤታማ አስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ ለማከናወን የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና መከታተያ ክፍል የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡

1. ከሙስና መረጃ አስተዳደር የሚመጡ መረጃዎች የአስቸኳይ የሙስና መከላከል እና የሙስናና ብልሹ አሰራር ይዘት ያላቸው፣በቂ ጥርጣሬ የሚያሳድሩ፣ በመረጃና ማስረጃ ላይ የተደገፉ መሆናቸውን አረጋግጦ መቀበል፣
2. በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት ልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች ወስጥ የተከሰቱ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ላይ ሥራወን የተመራለት ቡድን/ባለሙያ ሰነዱን በማንበብ በቂ ግንዘቤ ይወስዳል የሥራውን ባሕሪና እንዴት መሠራት እንዳለበት በጉዳየ ላይ ምላሽ ለመስጠት በኮሚሽኑ የተዘጋጁ አዋጆች ፣ደንቦች ፣መመሪያዎችን እና አሰራሮችን ያገናዝባል እንዲሁም በዝረዝር ከስራ ክፍሉ ጋር ይነጋገራል፡፡
3. የቀረበው ጥቋማ ጥናቱ በኮሚሽኑ ባለሙያዎች እንዲካሄድ ከተወሰነ የሥራ ሂደቱ ዳይሬክቶሬት/ቡድን ባለቤት ጥናት የሚደረግበት ተቋም/ ርዕሰ ጉዳይ ተገቢውን ግንዛቤ ከወሰደ በኃላ አፍስፈላጊውን የሙያ ስብጥር ያለበትን ጊዜያዊ የባለሙያዎች  ቡድን ይመሰርታል፡፡
4. ጥናቱን የሚያስተባብረው ቡድኑ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ቡድን/ በሚወከለው ባለሙያ ስለሥራው ባሕሪና እንዴት መሠራት እንዳለበት ከባለሙያዎቹ ጋር በዝርዝር ይወያያል ለዚህም  ያሚያግዝ ቼክ ሊስት የመተግበሪያ እቅድ/አክሽን ፕላን ያዘጋጃል ከቅርብ ሀላፊ ጋርም የጋራ በማድረግ ያጸድቃል፡፡
5. ሥራወን የተመራለት  ባለሙያ በተቋማት ውስጥ ስራውን ለመስራት የሚያስችል የግንኙነት ደብዳቤ በማዘጋጀት፣በኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊ በተዋረድ ባለው ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ፊርማ አማካኝነት  ግኙኙነት ይፈጥራል እንደ አስፋላጊነቱ በተቋም ከሚገኙ የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና የሥራ ሂደት ቡድን/ባለሙያ ለስራው ገለጻ በማደረግ በጥንቃቂ ስራውን በጋራ ይሰራሉ፡፡

urgent corruptin manal

6. ሥራው የተመራለት ባለሙያ ጥቆማውን መሰረት በማድረግ በተቋሙ ውስጥ ከሚመለከተው የሥራ ክፍል መሪ ወይም ሠራተኛ ላይ ከሥራውጋር አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎችይ ይሰበስባል፣የተሰበሰቡ መረጃዎችን ትንተና ያካሂዳል ፣ተገቢውን የአስተያየት ሪፓርት/ምላሽ በፁሁፍ ያዘጋጃል።
7. አጥኚ ቡድን በበቂ መረጃና ማስረጃ ላይ የተደገፈ፣ ጥራቱን የጠበቀና ወቅታዊ የሆነ ረቂቅ ሪፖርት ለቅርብ ኃላፊ ያቀርባል፣
8. በሪፖርቱ ላይ በቅርብ ኃላፊው አስተያየት የተሰጠባቸው ሀሳቦች ካሉ በድጋሚ የማስተካከል ሥራ መስራት፣
9. እንደአስፈላጊነቱ ወደ ተቋሙ በመሄድ በምክረ ሀሳቡ ላይ የመውጫ/exit/ ወይይት ማድረግ፣
10. የተስተካከለውን የመጨረሻ ሪፖርት/ምክረ ሀሳብ ለተቋሙ ለሚመለከታቸው ተቋማት /ስራ ክፍሎች ተደራሽ ማድረግ፣
11. የተሰጡ ምክረ ሀሳቦች መተግበራቸውን ወይም እየተተገበሩ ስለመሆናቸው ከሙስና ጥናት ትግራ ክትትል ጋር በቅንጅት መስራት፣
12. በቅንጅት የተሰራውን የሙስና ጥናት ክትትል ውጤት በመቀበል የተገኙ መረጃዎችን ሪፖርት በማዘጋጀት ለኃላፊ ማቅረብ አለበት።
13. ለጥናቱ የተሰሰባሰበው መረጃ ተጨባጭ ክፍተቶችን መኖራቸውን ከላመላከተ ሥራው የተመራለት ባለሙያ ተቋርጦ የነበረው እንዲቀጥል አጠቃላይ የውሳኔ ሃሳብ ሪፖርት በማዘጋጀት ለኮሚሽኑ /ለዳይሬክቶሬቱ/ለሥራ ሂደቱ ባለቤት ያቀርባል።
14. የቀረበውን የወሳኔ ሃሳብ ሪፓርት በመገምገም ከአመነበት ለኮሚሽኑ/ ለባላይ ሃላፊ አቅርቦ በመነጋጋር ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል ፣ለጊዜው የቆመ /የተቋረጠ ጉዳይ ካለ እንዲቀጥል ለተቋሙ ደብደቤ ይጽፋል።

## 3.3. የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት ሪፖርት ይዘቶች

የአስቸኳይ የሙስና መከላከል የጥናት ሪፓርት ሲዘጋጁ የሚከተሉትን ተግባራት በተዘጋጀው ሪፓርት ወስጥ መካተት ይኖርባቸዋል ፡፡

- → የጥናቱ ርዕስ
- → የተጠኚው ተቋም ስም

urgent corruption manal

- → ለጥናቱ መነሻ የሆኑ ፍሬ ነገሮች
- → በሚጣራበት ወቅት የታዩ ሰነዶች ጥሬ ሀቅ
- → በማጣራት ወቅት የታዩ መሰረታዊ ስህተቶች/ክፍተቶቸ ምንድናቸው? ግኝቶች
- → በማጥራት ወቅት የታዩ ችግሮች የሚያደርሱት ጉዳት
- → የችግሩ መንሴዎች
- → ችግሩን እንዲፈጠር ያደረጉ የስራ ክፍሎች
- → ለችግሩ መንሴኤ የሆኑ አመራሮች፣የስራ ሂደት አስተባባሪዎች እና ባለሙያዎች፣
- → አመራጭ የመፍትሔ ሃሳቦችን እና ጠንካርና ደካማ ጎኖቸውን
- → የማጣራት ስራውን ያካሄዱት ባለሙያዎች
- → የስራ ክፍሉ አስተያየት
- → የበላይ ኃላፊ

### 3.4. የጥናት ሪፓርቱን ለበላይ ሀላፊ ለውሳኔ ማቅረብ

1. ጥናቱን ያደረገው ዳይሬክተር/ቡድን/ባለሙያ የጥናት ረቂቅ ሪፖርቱን ለሚመለከተው የስራ ክፍል ኃላፊ ያቀርባል፣
2. በሚመለከተው የስራ ክፍል ኃላፊዎች የቀረበውን ረቂቅ የጥናት ሪፖርት በመገምገም ማሻሻያ የሚያደርግበት ከሆነ በዚሀ መሰረት መሻያ እንዲያደርግበት ያደርጋል፡፡
3. ረቂቅ የጥናት ሪፖረት በኮሚሽኑ አስተያየት መሠረት ከተሻሻለ በኃላ እንደ አስፋላጊነቱ ጥናቱን ከሚመለከታቸው ተጠኚ ተቋም የሥራ መሪዎች ጋር ወይይት ይደረግበታል በውይይቱ ላይ በተሰነዘሩ ሃሳቦችና አስተያየቶች መሠረት ሪፖርቱ ተስተካክሎ ለተቋሙ ይላካል፡፡
4. የጥናት ግኝቱ የሙስና ወንጀል ካላው በህግ ለመመርመርእና ለመክሰስ ስልጣን ለተሰጠው አካል ይላካል፡፡
5. የጥናቱ ሪፓርቱ በአሠራር ሥርዓቱ ውሰጥ ያሉ ጠንካራ ጎኖች መግለጽ ይኖርበታል፡፡
6. አስቸኳይ የሙስና መከላከል የጥናት ውጤትን የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀምና ማስረጃዎችን መሠረት በማድረግ የተከናወነው አስቸኳይ የሙስና መከላከል የማጣራት ስራ ዝርዝር ሂደት በሚያሳይ ሁኔታ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ሪፖርት ለተቋሙ የበላይ ሀላፊ ያቀርባል፡፡ የቀረበው የውሳኔ ሀሳቡ እንደተገኘው መረጃ እና ማስረጃ አንጻር ሊቀርብ ይችላል፡፡

urgent coruptin manal

7. የጥናት ሪፖርቱ እንደተጠናቀቀ ኮሚሽን እንደአስፋላጊነቱ ከተጠኚው ተቋም የስራ መሪዎች ጋር በሚያደርጉት ወይይት የድርጊት መርሃ ግብር ያዘጋጃል፡፡ የሚዘጋጀው የትግበራ የድርጊት መርሐ-ግብር ከሪፖርቱጋር አባሪ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የየማጣራት ስራው እንደቀረበው ጥቆማ ወይም በክትትል እንደተገኘው መረጃ ዓይነት ይዘት የውሳኔ ሃሳብ በሚከተሉት መንገዶች ሊቀርቡ ይችላሉ፡-
    1. ሙሉ በሙሉ ተሰርዞ በሂደቱ ተሳታፊ የሆኑ አካላት በላው ህግ አግባብ ተጠያቂ እንዲሆኑ በህግ ለመመርመርእና ለመክስስ ስልጣን ለተሰጠው አካል ይላካል፡፡
    2. እንደገና ከፍተቱ ተስተካክሎ ሂደቱ እንዲቀጥል እና በሂደቱ ተሳታፊ የሆኑ አካላት በላው ህግ አግባብ ተጠያቂ እንዲሆኑ በህግ ለመመርመርእና ለመክስስ ስልጣን ለተሰጠው አካል ይላካል፡፡
    3. የቀረበው ጥቆማ ወይም መረጃ ከሙስና እና ብልሹ አስራር ጋር ተያዥነት የሌለው ስለሆነ በተጀመረበት ሁኔታ እንዲቀጥል የሚል የወሳኔ ሃሳብ ሊቀርብ ይችላል፡፡

urgent coruptin manal

# ክፍል አራት

## 4.የኮሚሽኑና የተቋማት የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ተግባርና ኃላፊነት

### 4.1.የኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነት

1. በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የመንግስት ልማት ድርጅቶች እና የህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ሙስና ለመፈፀም በዝግጅት ላይ ያለን ጉዳይ ድርጊቱ ወደ ሙስና ከመለወጡ በፊት የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራ በትኩረት እንዲሠራ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ግንዛቤ በመፍጠር ያቅዳል፤
2. ኮሚሽኑ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የመንግስት ልማት ድርጅቶች እና የህዝባዊ ድርጅቶች አፈፃፀም ሂደት ላይ ለሚቀርቡ ጥቆማዎች የአስቸኳይ መከላከል ሥራዎች ሊሰራባቸው የሚችሉ ጉዳዮች ሆነው ሲገኙ ይህንኑ የማጣራት ስራ ይሰራል፣ የማሻሻያ ምክረ ኃሳብ ያቀርባል፣በጥናቱ መሰረት የተመላከቱ ክፍተቶች ተግባራዊነትን /ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፣
3. በአስቸኳይ የሙስና መከላከልም ሆነ በብልሹ አሰራር ጥናት ሂደት ውስጥ የተገኙ የሙስና ወንጀል ፍሬ ነገሮችን ሲኖሩ በሕግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ላለው እና አግባብነት ላለው አካል እንዲላክ ያደርጋል፣ መረጃዎችን ያመቻቻል፤ይከታተላል፣ ለጠቋሚዎች መላኩን ያሳውቃል፣
4. በአስቸኳይ የሙስና መከላከል የዳነ ሀብት መረጃን ያጠናቅራል፤ ለህዝብ ተደራሽ ያደርጋል፣ ለጥናትና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳይ ጥቅም ላይ እንዲውል መረጃ ይሰጣል።
5. ከተሰሩ የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራዎች ውስጥ የአስተማሪነት ይዘት ያላቸውን ጉዳዮች በመለየት የምርመራ ጋዜጠኝነት ስራ እንዲሰራባቸው ያደርጋል፣
6. ሌሎች የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ መርሆና ዓላማን ሊያሳኩ የሚችሉ ተግባራትን ያከናውናል።

urgent coruptin manal

## 4.2.የተቋማት የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ተግባርና ኃላፊነት

1. ኮሚሽኑ እንደአስፈላጊነቱ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራን የሚመለከት ጥቆማ ሲደርሰው ለተቋማት የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ያሳወቃል፣ተጣርቶም እንዲቀርብለት ያደርጋል፣
2. ጥቆማውን የተቀበለው የተቋም የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የደረሰውን ጥቆማ አጣርቶ ውጤቱን ለኮሚሽኑ ያሳውቃል፣
3. በተቋሙ የተጀመሩ አስቸኳይ የመከላከል ሥራዎች የደረሱበትን ደረጃ ይከታተላል፣
4. የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ ለመሥራት የተቸገረባቸዉ ሁኔታዎች ሲኖሩ ከተቋሙ ኃላፊዎች ጋር በመነጋር እልባት ይሰጣል፣ እንዳስፈላጊነቱም ለህግ አስፈፃሚ አካላት ሪፖርት ያደርጋል፤
5. የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ ለሚጠይቀው የእገዛ ጥያቄ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

urgent coruptin manal

# አባሪዎች

## የጥናትማድረጊያቅጽ፣የሪፓርት ቅጽ፣ተጠያቂ

### አባሪ-1.የጥናት ማድረጊያ ቅጽ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት ቅጽ

1. የጥናቱ ርዕስ ------------------------------------------------------------------------------------
2. የተጠኚውተቋም ስም ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
3. ለጥናቱ መነሻ የሆነው ፍሬ ነገሮች ------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
4. በሚጣራበት ወቅት የታዩ ሰነዶች (ጥሬ ሀቆች) ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
5. በማጣራት ወቅት የታዩ መሰረታዊ ስህተቶች (ግኝቶች)---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
6. በማጥራት ወቅት የታዩ ችግሮች የሚያደርሱት ጉዳት ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
7. የችግሩ መንሴዎች ----------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------
-------

8. ችግሩን እንዲፈጠር ያደረጉ የስራ ክፍሎች ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

9. ለችግሩ መንሴኤ የሆኑ አመራሮች፣የስራ ሂደት አስተባባሪዎች እና ባለሙያዎች፣ ----------------------------------------------------------------------------------------------

10. አመራጭ የመፍትሔ ሃሳቦችን እና ጠንካርና ደካማ ጎኖቸውን ----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

11. የማጣራት ስራውን ያካሄዱት ባለሙያዎች---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

12. የስራ ክፍሉ አስተያየት -----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

13. የበላይ ኃላፊ ------------------------------------------------------------------------------

urge

## አባሪ 2. የሪፓርት ማድረጊያ ቅጽ

| በአስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ የዳነ የመንግስትና የሕዝብ ሀብት፣ | | | ተጠያቂ የሆኑ ግለሰቦች (አመራር፣ ፈጻሚ፣ደላላ ፣ሌላ) | | | | ተጠያቂ የተደረጉበት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | የህግ | የአስተዳደር | የፖለቲካ |
| በገንዘብ (በብር) | በአይነት | መሬት | የተጠያቂዎች | ወ | ሴ | ድ | | | |
| | | | አመራር | | | | | | |
| | | | ፈጻሚ | | | | | | |
| | | | ደላላና ሌሎች | | | | | | |

## አባሪ 3. ተጠያቂ የሆኑ የመንግስት አመራሮች፣ሰራተኞ

| የተቋሙ ስም | ተጠያቂ የሆኑ ግለሰቦች | አመራሮች፣ | | | ቅጥር ሰራተኞች፣ | | | ሌሎችን የህ/ስብ ክፍሎች | | | አጠቃላይ ድምር | | | በዲስፕሊን | | በወንጀል ተጠያቂ የሆኑ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | | ቀላል | ከባድ | | |
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት |
| 1 | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5 | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6 | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 7 | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |

### አባሪ-4 በአስቸኳይ የሙስና መከላከል የዳነ ሀብት የሚሳለበት አግባብ

በአንድ የግዥ ሂደት በጨረታ የተቀመጠው ዋጋ ጨረታው በሚወጣበት ወቅት በገበያ ላይ ከነበረው ዋጋ ጋር በተነፃፃሪ የሚገኘው የዋጋ ልዩነት በሚመለከተው የመንግስት አካል በሚገኝ መረጃ መሰረት የሚታወቅ ሀብት መስረት ያደረገ ሲሆን ሌሎች በዓይነት የሚገለፁ እንደ መሬት በሊዝ መመሪ መስረት እዲሁም በከተማ አስተዳደሩ በከቤ ወሳኔ መሰረት ለቦታው በካሬ ሜትር አማካይ የጨረታ ዋጋ የሚሰላ ሲሆን ከመሬት ወጭ ያሉት ደግሞ በገበያ ሊኖራቸው በሚችለው ዋጋ የሚገመት ወይም የሚሰላ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ( ቤት፣የግንባታ እቃቆች፣መከኒናዎች እና ብረታብረቶች etc)

### አባሪ-5. የአስቸኳይ ሙስና መከላከል የጥናት የጊዜ ስታንዳርድ መነሻ

manal

| ተ.ቁ | አገልግሎት አይነት | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚያከናውነው አካል | ስራው የሚወሰደ ውጊዜ በስዓት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የዝግጅት ስራ | የቀረበ ጥቆማ መረከብ ፣ | ቡድን መሪው | 15 ደቂቃ | |
| | | እግድ ማዘጋጀት | የስራ ክፍሉ | 20 ደቂቃ | |
| | | አጠቃላይ ስለ ማጣራቱ ጉዳይ በስራ ክፍሉ ወይይት ማድረግ፣ መረዳት፣ የድርጊት መርሐ ግብር ማዘጋጀት፣ | ቡድን መሪናባለሙያ | 4 ሰዓት | |
| 2 | ጥናት ወይም ማጣራት ማካሄድ | ጥቆማ ወደ ቀረበበት ተቋም በአካል በመሄድ ስለጥናት ስራው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመገኛኘት ስለስራው ግንዛቤ መፍጠር፣ ለማጣራቱ ስራ ተገቢነት ያላቸውና ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ | ቡድን መሪናባለሙያ | 40 | እንደ የጥቆማ ው ባህሪ የሚለያይ |

| ተ.ቁ | አገልግሎት አይነት | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚያከናውነው አካል | ስራው የሚወሰደ ውጊዜ በስዓት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | ሪፖርት ማዘጋጀት | የተበሰበውን መረጃ በመተንተን ለሪፖርት ብቁ ማድረግ፣ | ቡድን መሪናባለሙያ | 4 | - |
| | | ተተንተኖ ብቁ የሆነውን መረጃ በሪፖርት መልክ ማዘጋጀት፣ | ቡድን መሪናባለሙያ | 8 | - |
| | | የተጠናቀቀውን ሪፖርት ለተቋሙ በማድረስ እንደጉዳዩ ሁኔታ የመውጫ ወይይት ማድረግ፣ | ባለሙያ | 4 | - |
| | | የሙስና ወንጀል ባህሪይ ያላቸውን በመለየት ለሚመለከተው አካል መላክ፣ | ባለሙያ | 30 ደቂቃ | |

urgent corrup

## ማጣቀሻዎች


- → የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስነ-ምግባር እና ጸረ ሙስና ኮሚሽን መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 75/2014 ዓ/ም
- → የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላል አስራር ደንብ ቁጥር 11/2015
- → የሙስናወንጀሎች ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 881/2007
- → የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ አፈፃፀም መመሪያ መመሪያ ቁጥር 21/2013
- → የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ምርመራ የማሰልጠኛ ሞጁል
- → TRAN SPARANCY INTERNANTIONAL BEST PRACTICES FOR PREVENTIVE ANTI-CORRUPTION BODIES April 2015
- → UPDF THE ACTION RESEARCH GUIDEBOOK 2019


urgent coruptun manal